# ለመጠናከር ፅዳት፤ ፅዳት ደግሞ ቅድሚያ ከራስ

*ሀማ ቱማ*

በፖለቲካ ዓለም ብዙ ለቆየነው ምናልባትም እየከበደ ይሆናል ግን የትላንት ወያኔ የዛሬ ፃድቅ መሆኑን ማመኑ ፍፁም ያዳግተናል። ታምራት ላይኔ ከወያኔ ወደ ጳንቱ በከርቸሌና ቃሊቲ ተጉዞ ደረሰ የሚለውን ስንሰማ አይ ጉድ ሰውየው በስዊስ ባንክ አሁንም በስሙ ያለውን 8 ሚሊዮን ዶላር ሊወስድ መውጣት ፈልጎ ነው ብለን መደምደሙ ይቀናናል። የእናት አባቱን ሀይማኖትም ክዶ መንጎዱ ራሱ ያው ኢሕአፓን ክዶ ወያኔ እንደሆነው ሁሉ ለምዶበት ነው ብለን የምናልፈው ሊሆን ይችላል። ታምራት ፍቅር ፍቅር ሲል ለሰረቀው ገንዘብ መሆኑ አያከራክርም። በጣም ያሳዝነህ ጉዳይ ሲባል ሻዕቢያና ወያኔ መጣላታቸው ነው ማለቱ ራሱ በቂ ነው። ያቆሸሸ ሰይጣን ጭራሽ ሳያበሻቅጥ አይለቅም።

ታምራት ላይኔ ከነገ የኢትዮጵያ ታሪክ አንፃር ሚዛኑ ገለባ ነው። ለወንጀሉ ንስሐ እስካልገባ ድረስ መጠየቁ የማይቀር ሊሆን ቢችልም የሰውየው ምዕራፍ ተዘግቷል። በእርግጥ ቀደም ያኔ ያኔ ኢሕአፓ በመግባረ ብልሹነቱ አባሮት በነበር ተገላግለን ነበር። በዚህ ያነሳሁት መሰሎቹንም በተመለከተ መባል ያለበትን ለማለት ብቻ ነው። ለምክንያት ድመት ሞተች እንዲሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ተጠናክሮ ለድል እንዲበቃ ከድከመቶቹ መላቀቅ አለበት። ይህ ደግሞ በቅድሚያ እነዚህ ችግሮችና ድክመቶች ምን እንደሆኑ በጥሞና መመርመርን ይጠይቃል።ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር ነውና ተቃዋሚ የተባለው ጎራ ያለውን ድክመቱን ማስወገዱ ወሳኝ ነው። በወያኔ ላይ የማያዳግም ድልን የምንመኝ ሁሉ በራሳችን በተቃዋሚው ጎራ ያለው ችግርና ድክመት ላይ የምናተኩረው ይህ ካልተወገደ ወደ ድል ለመጓዝ ባለመቻሉ ነው። ጠላት የሚያውቀውን--ያውም ብዙ ጊዜ ራሱ ጠላት የፈጠረብንን--ድክመት ደብቆ የሰጎን ፖለቲካን መከተሉ ወደ ገደል የሚከት ይሆናል። ለዚህም ነው በዚሁ በሕዝብ ጎራ በምንለው ውስጥ ባለው ችግር ላይ ትኩረት ሰጥተን የላላውን መወጠር የምንፈልገው። የተቃዋሚው ጎራ በቅድሚያ መፅዳት አለበት። ወያኔ የፅዳት ዘመቻ እያለ ሰው ይጨርስ እንደነበረው ዓይነት ሳይሆን ማን ተቃዋሚ፤ ማን ደግሞ ተቃዋሚ ነኝ እያለ ተቃዋሚን ተቃዋሚ እንደሆነ መለየት ያስፈልጋል ማለት ነው። የሕዝብ ጎራ ውስጥ ተኩላውም በጉም፤ጊንጡም ንቡም ከተተረማመሰ ጠላትን መጋፈጡ ቀርቶ ከወዲሁ ወዳጅ ነኝ ባለው መነደፉና መደናቀፉ ይከተላል። በየድርጅቱ ብቅ ያሉት አንጃዎች፤ከሆዳቸው አርቀው ማስተዋል ያቃታቸው ጉዶችና የሕዝብን ጎራ ለወያኔ አጋልጠው የሰጡ አስመሳዮች፤ ዛሬም ሕዝብን የሚበጠብጡት ሁሉ የትግላችን ፀር መሆናቸው ታውቆ መገለል አለባቸው።

ክላሺን ታጥቆ፣ ቁምጣውንና ትጥቁን አሳምሮ ላይ ታች ያለው ሁሉ ጀግና ወይም ቆራጥ ተዋጊ እንዳልነበር በሰፊው ያየነው ነውና አስመሳዮችና ሰርጎ ገቦችን ብቻ ሳይሆን የተሳሳተ መስመር የያዙትንም በየጊዜው በማጋለጣችንና በመውቀሳችን በክብር ነክ ሊወነጅሉን የተነሱ ብዙዎች ናቸው:: በድርጅት ጉዳይ ጣልቃ ገቡ፣ እገሌና እገሊትን ለመተቸተ ደፈሩ ተዳፈሩ፣ ከፋፈሉ ወዘተ ብለው የጮሁና የክህደቱን አውራ ያውም ሀገራችን የጀግና ምሳሌ የጠፋ ይመስል ሀገሮች አቋርጠው ሄደው ማንዴላ ብለው የሰየሙና የሕዝብ ጎራ እንዳይፀዳ የታገሉ ነበሩ፣አሉም :: ግን ስርዓቶችና አገዛዞች ላይ ካመፅን ዘንድ በዚሁ ጩኸት ተደናግጠን ወደ ዝምታ አልተወረወ ርንም:: በግለሰብ ተንኮልና በሌሎ ድርጅት ተቃውሞ የሚፈርስ ድርጅት ደግሞ ገና ከመጀመሪያ ው ወስጣዊ ድክመት አለው ማለት ነው:: ይህም ሊያነጋግር የሚችል ነው:: ስንል የነበረው ደረሰ ብለን በደረሰው--ግን ልናልፈው እንችል በነበረ --ውድቀት ደስ ባይለንም ድንገተኛ የሆነብን ችግር ግን አለመኖሩን ማወቅ ማመን ያስፈልገናል:: ኢሕአፓ ለምሳሌ አንጃንበውስጡ ይዞ ሲሽመደመድና ሲጎዳ ዓመታት በማለፉ ግልግሉ ሲመጣ ያላወቁት ተገረሙ እንጂ ለአባላቱ ያልተጠበቀ  አልነበረም:: በ1997 ግንቦት--ሰኔ ወያኔ በህገወጥ መንገድ የሕዝብን ድምፅ ሰርቆ በአፈናና ጭፍጨፋ በስልጣን መቆየቱ የሚገመት ከመሆኑ ሌላ ቅንጅትና ህብረት ራሳቸው በነበራቸው ውስጣዊ ይዘት በአንድነት ሊዘልቁ እንደማይችሉ ምስጢር አልነበረም:: ሳይውል ሳያድር አስመሳዮቹ ወደ ወያኔ ሲጠጉ ሌሎቹ ደግሞ /ቅንጅትም ህብረትም ውስጥ የነበሩት/ አንድነታቸውን ጠብቀው ሊሄዱ አልቻሉም:: ዛሬ የምናየው ሁኔታ እውነት ይነገር ከተባለ ዱብ ዕዳ አይደለም:: ላይሆን የቻለው ግን ያለውን የፖለቲካ ሁኔታ በጥሞና መርምረን ድክመት ጥንካሬን በጊዜ ስንቃኝ ብቻ ነው::  ከሕዝብ ትግል አንፃር ታማኝነታችን ለሕዝብና ለትግሉ መሆን አለበትና የተበላሸውን በጊዜ ተበላሸ ማለቱ ቅንጦት ሳይሆን ግዴታ ነው::

የፖለቲካው ዓለማችን ጥራዝ ነጠቅነት እየተጠናወተው መሆኑ ድብቅ አይለደም:: ስራ ለመቀጠ ር ማመልከቻ አስገብተው ለውይይቱ ተዘጋጅተው የሚሄዱት ሁለ ወደ ፖለቲካው ድንገት ዘው ሲሉ  አለማወቅን ማስቀደም ያለባቸው ይመስላቸዋል ቢባል ስህተት አይሆንም:: ስለ ድርጅትም ሆነ ስለ ትግል፣ ስለጠላትም ሆነ ሕዝብ ግንዛቤያቸው ኮስማና ሆኖ ሳለ በመማር ፈንታ አስተማሪ ሆነው በሕዝብ ላይ አዋቂ ነን ብለው ይሰየማሉ:: ፖለቲካው የሞት ሽረት ጉዳይ የሆነበት ወያኔ ቢያንስ በተንኮሉ የተካነ ነውና እነዚህን ዓይነት መጤ ፖለቲከኞችና ሆዳሞቹንም በየተራ እያስተ ናገደና እያደናገረ ያስኬዳቸዋል:: ተቃዋሚ በሉን ብለው በወያኔ ጫማ ስር ወድቀው ያሉትን ማየቱ ይበቃል:: ባዕድ ሀገር ደግሞ የወያኔ ፀር ነን እያሉ ዋናው ትኩረታቸውና ተልዕኮአቸው አንድነት ሀይሎችን ማጥቃት ሆኖ የሚገኙትንም ማየት እንችላለን:: በፖለቲካ ፓርቲና በማህበራትም ደረጃ ተደራጅቶ ሕዝባችን ሲታገል ብዙ ብዙ ዓመታትን ያስቆጠረ ሆኖ ሳለ ወደ ኋላ ሊመልሱትና ዳግም በስህተቶች አንደዘፈቅ ሊያደርጉት ይጥራሉ:: በቅርቡ ለምሳሌ ለሕዝብ ትግል መሪ ድርጅቶች አያስፈልጉትም በሚል አወቅን ብለው የተውገረገሩትን ማንሳቱ ይበቃል:: በዚያውም ቀጥለው በአስቸኳይ የስደት መንግስት ይቋቋም ብለው ከበረሃ ጦር ይዘው ወይም

ከጠንካራ አቅም ተነስተው ሳይሆን በባዶ በባዕድ ሀገር ሲጮኹ ምነዋ በትግሉ ቀለዳችሁ ማለቱ የግድ ነበር፡፡ ሕዝብ በራሱ ተመክቶ እንዳይታገል ተው ጠብቅ አሜሪካን ለምንና ነፃ ያወጡናል፤ ለአሜሪካ እንፀልይ፤አቤት እንበል ወዘተ እያሉ የሰበኩትንም የነጭ ቡችላ ማፈሪያዎች ማለቱ የግድ ነበር፡፡ ወያኔን ወያኔ አትበሉ፤ጠላት አትበሉት፤ አብረናቸው መኖር አለብን ወዘተ በሚልም የሕዝብን ቁጣ ለማለዘብና አድርባይነትን ለማስፈን የተነሱትንም እንዲሁ መታገል ግዳጅ ሆኗል፡ አስፈላጊ የጥራት ትግሎች ነበሩ፤ ናቸውም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ማለትም የወያኔ አገዛዝ በመጀመሪያ ደረጃ የተደራጀና አረመኔ ቡድን እንደመሆኑ መጠን ከከይሲ ግቡ ለመድረስ በትኩ ረት የሚንቀሳቀስ ነው፡፡ በትርፍ ጊዜ ፖለቲከኞች ወይም በጥራዝ ነጠቅነት በተበከለ ትግል የሚሸነፍ አይደለም፡፡ አንድ ዓላማና ግልፅ ግብ ይዞ በቆራጥነት የሚንቀሳቀስ ሀይል ካልገጠመው በቀር አይሸነፍም፡፡ ለዚህም ነው የትግሉን ጎራ በውዠንብር የሚያደናግሩትን ወይም ክንዱን የሚያላሉትን ሁሉ መቃወምና መርዛቸውን እንዳይረጩም ማገድ ያለብን ማለት ነው፡፡ ይህም የትግሉ ዋና አካል ነው፡፡

በተቃዋሚ ስም ተቃዋሚውን የሚያጠቁ ወይም ያለውን አገዛዝ በአዲስ መልክ ሊያስቀጥሉ የሚሯሯጡ መኖራቸው ደግሞ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ቢከፍቱት ተልባ ማለት እስካልቻልን ድረስም ጉዳቱ ይበዛል፡፡ " ብዙ ሀሰተኞች ነቢያትም ይነሳሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ" እንደተባለ ው ዛሬ በሀገራችን ሀሳዊ መሲሖች ፈልተዋል፡፡ ደፍረው ፀሐይን በቀኜ ጨረቃን በግራ እጄ ይዤ ላችኋለሁ ባይሉንም  በእኛ መንገድና በእኛ መሪነት ዴሞክራሲን ትላበሰላችሁ ማለታቸው ግን አልቀረም፡፡ አንዳንዶች በድርጅቶች መሀል ያለውን መሰረታዊ የፖለቲካ ግብና ይዘት ልዩነት ለማወቅ ምንም ጥረት ካለማድረጋቸው ሌላ ሁሉም አንድ ናቸው ብለው በደፈናው ይደመድማሉ ፡፡አንድ ወይፈን የቀላቀለ ከብቶቻችን ይላል ሆኖ ራሱን ተቃዋሚ ካለና ዴሞክራሲ የሚለውን በመርሀ ግብሩ ካሰፈረ ዴሞክራሲያዊ ነኝ ብሎ ሲሞካሽ የነገሮች ውል ይጠፋል፡፡ አረና በሚል ድርጅት ስም የተሰባሰቡት ከመለስ የተጣሉ ወያኔዎች ለምሳሌ የወያኔን ጠባብና ዘረኛ አገዛዝ በአዲስ መልክ ለመቀጠል ያላቸውን ዕቅድ ነው ዴሞክራሲና አዲስ ብለው ሊጭኑብን የሚሞክሩት፡፡ ይህን እውን  እንዲያደርጉ  ሕዝብ ከሞት አጠገብ የሆነ እንቅልፍ እንዲያንቀላፉ ይፈልጋሉ፡፡ ነቅቶ ከሆነ ስለማይቀባላቸው የእንቅልፍ ልቡን ነው የሚፈልጉት፡፡ አጋሮቻቸው መገናኛ ብዙሀን-ድረ ገፆችም ጭምር--በማደንዘዣነት ተሰልፈው ይረዷቸዋል፡፡ በአንድ ወቅት አንድ ቀንደኛ የወያኔ መሪ የነበረ ዛሬ የሕዝብ ነፃ አውጪ አርበኛ ተብሎ ሲሞገስ እንደነበርና የጓዶቻቸውን ደም የረገጡም ጉዶች ሳይቀሩ ሲያዳንቁት እንደነበር ታዝበናል፡፡

ለይቶ ማወቅና ማን ለሕዝብ ማን ለራሱ ወይም ለሕዝብ ጠላት እንደቆመ ማጣራት ተገቢ ነው፡፡ በዚሁ መልክ ጥረት ሲደረግ የጥላቻ ፖለቲካ ሰበካ ተያያዛችሁ ብለው ወቃሾች አልጠፉም፡፡ የሕዝብ ጎራ መጥበብ የለበትም፤ይስፋም ይሉናል፡፡ ጉዳዩ ከጥላቻና ጥበት ጋር ግን የተያያዘ አይደለም፡፡ ከእጅ አይሻል ዶማ መሆኑ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ትብስን ማግባት እየሆነ ነው ያስቸገረው፡፡ የሕዝብ ጎራ ሰፍቶ ጠንካራ የሚሆነው ሕዝባዊና ሀቀኛ በሆኑ ሀገር ወዳድ ሀይሎች

ሲታጀብ እንጂ አስመሳዮችና ተለጣፊዎችን ሲያቅፍ አይደለም፡፡ የወያኔን አሰራርና ተንኮል ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ጠመድኩት ጠላሁት ብሎና ዝዋይ ለአንድ ወር አሰርኩት ብሎ ቅጥረኛውን ተቃዋሚ አስመስሎ ትግሉ ላይ ጭኖ ነበር፡፡ ዛሬ ተቃዋሚ ነን ብለው ግን መመሪያ ከወያኔ የስለላ ቢሮ ወይም ከባዐድ የሰላላ መዋቅር የሚቀበሉ መሪዎችና አባላት የሞሉባቸው እንዳሉ ምስጢር አይደለም፡፡ ራሰን ማወቅ፤ጠላትንም ማወቅ የተባለውን ማሰታወስ ያሻል፡፡ቀደም ሲል ወያኔ ወያኔ ነቱን ሳይለውጥ ኢሕአዴግ የተባለ ጭምብል በመልበሱ ብዙ ዜጋ ተደናግሮ እንደነበር ሀቅ ነው፡፡ እስከ መጨረሻ የደም ጠብታዬ ያለው ኮለኔልም ገና ሳይደማ የሚሰርቀውን ሰርቆ ዚምባብዌ ተጠቃሏል፡፡ ከሕዝብ ጎን እንቆማለን ያሉትም ቀጠል አድርገው ግን መጀመሪያ ወያኔ ፓርላማ ገብተን የሚለውንም አስደምጠውናል፡፡ ቃል ማደናገሪያ፤ ወናፍ ፕሮፓጋንዳ፡፡ ዛሬም በወያኔ የመጪው ምርጫ እንሳተፋለን፤ብረት ያነሳ ውጉዝ ከመ አርዮስ ይሁን የሚሉን በወያኔ ላይ እርም ት ሳይሆኑ እሱኑ አጃቢዎች ናቸው፡፡ ዛሬ በስድብ ገመድ በአደባባይ ሊሰቅሉን ኡኡ የሚሉ ክፍሎች እሳቸው የሚሿቸውንና ካባ ያለበሷቸውን ግለሰቦች እንዳንተች ሲከላከሉ ቆይተው ዛሬ ደግሞ እነዚህኑ ግለሰቦች ወደ ብልግና በተጠጋ ደረጃ ሲዘረጥጡ ና ሊያዋርዱ ሲቃጡ ማዳመጥ ተገደናል፡፡ በመሰረቱ ፖለቲካዊ ትችትና ስድብን መለየት ያቃታቸው ክፍሎች ድርጅቶችም ሆኑ መሪ ነን ያሉ ግለሰቦችም ከሕዝብ ትችትና ወቀሳ በላይ አለመሆናቸውን መገንዘብ አቅቷቸዋ ል፡፡ ራሳቸውን በራሳቸው አንቱ ያሉና ከእኛም በላይ አዋቂ ለአሳር በሚል ሕዝብን የናቁ ደግሞ ወኔም፤ፅናትም ህዘባዊነትም ሲጠፋባቸው ድንቁም ምሁር መባላቸው በክፉ ተወስዶ ሊተቹ የደፈ ሩትን በፀረ ምሁርነት ከሰዋል፡፡ አንጃን አንጃ ማለት ስድብ ሳይሆን አቅዋምና ሚናን መግለጥ ነው፡፡ አሳፋሪ የሆነው አቅዋም ነው መታረም ያለበት እንጂ ዘረኛን ዘረኛ፤ ጠባቡን ጠባብ ፤አንጃ ን አንጃ፤ባንዳን ባንዳ፤ የፈረንጅ ቅጥረኛውን የፈረንጅ ቡችላ ማለቱ አይገባም ማለት ትክክል አይደለም፡፡ የሀገርና የሕዝብ የነገ ዕጣን የሚወስን ትግል ተያይዘን እያለ እነ እሳቸው በሉን ቅር ይላቸዋል በሚል የግለሰብን ግብዝነት ልናስቀድም ልናሽሞመነሙን መጠበቅ የለበትም ማለት ነው፡፡

ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናይ ለምሳሌ ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ጥቅም ሆነ ለሕዝቦቿ ደህንነት የማይበ ጅ ግን ግንጠላን ለሚያቀነቅኑት መሳሪያ የሚሆን ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የተባለ ስብስብ የተመሰረተ ጊዜ ኢሕአፓና ሌሎችም ይህ ተቋም ለሕዝብ አይበጅም በማለታቸው የደረሰባቸው ን ውርጅብኝ እናገኛለን፡፡ የዚህ ተቋም ፅኑ ተሟጋቾች ዛሬ ተቃዋሚዎቹ ሆነው ሲገኙ ለትናንቱ ዘለፋቸውና ክሳቸው ግን ይቅርታ ሲጠይቁ ገና ለማዳመጥ አልታደልንም፡፡ ዛሬ ወያኔ በህገወጥ መንገድ ለእስር የዳረጋትን የድርጅት መሪ ትላንት በምን ደረጃ ሲያወድሷት እንደነበርና ከዚያም በምን ደረጃ እንደዘለፏት ደግሞ የታዘብነው ነው፡፡ በእኛ በኩል በአቅዋም ደረጃ የተቸና ቸውን በግል ደረጃ ወርደን ስንዘልፍ የታየን አይደለንም---ሌሎች ግን ይህን ማለት የሚችሉ አይደሉም፡፡ መለስን አረመኔ፤ጠባብ፤ ወሮበላና ሌባ ስንለው ሰደባችሁት የሚሉን ካልሆነ በስተቀር፡፡ በዕብሪት የተወጠረን ደግሞ በሀቅ ትችትና በሂስ ተንፈስ ማድረጉ ይጠቅማል እንጂ

አይጎዳም። መንግስቱ ኃይለ ማርያም ከእኔም በላይ አዋቂ ለአሳር ወይም የሹም ዶሮ ነኝ ማለት ገና ሲጀምር በጠዋቱ ረጋ በል እንጂ ምነዋ ብሎ ሀቁንና ልኩን የሚነግሩት ደፋሮች አግኝቶ በነበር ምናልባትም እንዲያ ታብዮና ተገብዞ አይጓዝም ነበር። የእነ እገሌ ብሎ እነዚህኑ መጥራቱ ከማክበር ደረጃ ሊቆጠር ስለሚችል በዚሁ እንለፈው እንጂ ይህ የፖለቲካውን መድረክ ያፈነው ጥራዝ ነጠቅነት ለወያኔ በተለይ ክፍትና ለም መደረክን እንደሰጠው ማወቅ ይኖርብናል። በድጋፍና ዘለፋ ሽፋን ወያኔ ሊያጠፋቸው በሚፈልጋቸው ግለሰቦችና ሀይሎች ላይ በግልፅ በራሱ ሎሌዎችም ሆነ በስውር አጫፋሪዎቹ ለመረባረብ አመችቶታል። ቀደም ሲል ባወጣው የ 52 ገፅ የምስጢር መመሪያ ያሰፈረውም ይህንኑ ነው--ዛሬ ወያኔና መሰሎቹ በየትኞቹ ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ተረባርበዋል ብሎ መመርመሩ ብቻ በቂ ነው። ስህተቶች እንዳይታረሙ አትናገሩ፣ ትችት ሲደረግ ውግዘት፣ ትችት ብሎ ዘለፋ፣ በግለሰቦች ላይ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻን ማካሄድ-- ይህ ሁሉ ወያኔ ወያኔ ቢሸት የሚያስገርም አይደለም። በፀረ ወያኔ ግለሰቦችና ድርጅቶች ላይ ብቻ አተኩረው የሚንቀሳቀሱ ድረ ገፆችና ፓልቶኮች የፈሉት አለምክንያት አይደለም።

ወደ ግለሰቦች ቦታና ሚና ስንመጣም ቢያንስ የኢሕአፓ እምነትና ተመክሮ እስከጠቀመ ድረስ ሊጠቀስ የሚችል ነው። ኢሕአፓ--ማለትም የጥንትና የዛሬ አንጃዎችን ሳይጨምር--በጋራ አመራር ያምናል። አመራር ቦታ መርጠው አባላት የሚያስቀምጧቸው መሪዎች የሚሰሩት በጋራ ነው። የግለሰቦች አስተዋፅዖና ሚና የሚበረታታ ቢሆንም አንድ ግለሰብ ሁሉን አድራጊና ፈጣሪ ተብሎ መወሰዱ የአባላትን ሚና የሚያጫጫና ክብራቸውንም የሚነካ ነው ብሎ በማመኑ የድርጅቱ ሊቀመንበርና ብቸኛ መሪ የሚለውን አልተቀበለውም። በተመክሮ ደረጃም ድርጅቱ በ1964 ዓ.ም. ሲመሰረት ዋና ፀሀፊ የተባለው ግለሰብ ባለስልጣን ነኝ ብሎ መረን ስለለቀቀና የራሱንም ተክለ ሰብ ለመትከል ሲሯሯጥ ስላስቸገረ--ውሎ አድሮም ያልኩት ካልሆነ ባይ አንጃ በመሆኑ--ድርጅቱ አይተነዋል ጠልተነዋል ብሎ የተወው ጉዳይ ነው። የአንድ መሪ ቀርቶ የአንድ ድርጅት ራሱ ገኖ የሕዝብን ሚና መቀማቱ ትክክል ባለመሆኑ ኢሕአፓ ያለው አቅዋም ሕዝብ አንድ መሪ (ቆራጡ ሊቀመንበር ዓይነት!) ያስፈልገዋል የሚል ሳይሆን የሚያታግለው ድርጅትና ሚናውን በሚገባ እንዲጫወት የሚያስችለው ድርጅት ነው ለሕዝብ የሚበጀው የሚል ነው። በዚህ ሂደት ሕዝብ በቆራጥነታቸውና ብልህነታቸው አክብሮት ሰጥቶ መሪነታቸውን እያፀደቀላቸው የሚሄዱ ዴሞክራሲያዊና የጋራ አመራርን የማይቃወሙ መሪዎች ከወጡ ደግ ይሆናል ማለት ነው። የሆነ ግለሰብ መሪ እኔ ብቻ ስላለ ወይም ቅንጣት መከራ ሳይቀበልና ውጣ ውረዱን ሳይችልና በእሳት ሳይፈተን የትግሉ መሪ (ያውም በሩቁ!) በሉኝ ስላለ እውነትም መሪ ሊባል ይገባዋል ማለትም አይደል። በመሆኑም ኢሕአፓ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ተክሰለሰብ ዝንባሌዎችን ታግሏል፣ተቃውሟል። የግለሰብ ዝናና አልፎም ከሁሉም በላይ አዋቂ ብሎ መሰየም ዴሞክራሲያዊ አሰራርን ይፃረራል። መንግሰቱ መለስ ኢሳያስ ማለት ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚ ድርጅት ውስጥም ቢሆን የአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭነት የሰፈነባቸውንም ይመለከታል። ከዚያ እንደ ሰሜን ኮሪያና ሶርያ ንጉስ ሳይባሉ ፈላጭ ቆራጭ አፄዎች ይፈጠሩና ቦታቸውንም ለልጆቻቸው ያወርሳሉ። ለዚህ ዓይነት ስርዓት ምስረታ የአንድም ዜጋ ደም ጠብታውም መፍሰስ የለበት

ም ብሎ ኢሕአፓ ስለሚያምን ከሕዝብና ከሕዝብ ትግል በላይ ሆነው በፈላጭ ቆራጭነት ሊሰየሙ የሚዳዱትን ሁሉለዴሞክራሲ እንጂ ለግለሰብ ስልጣን አልታገልም ይላቸዋል:: ከዚህም ተያይዞ ማንኛውንም የተቃዋሚ የድርጅት መሪ በአግባቡ ቢያከብርም ከሕዝብ ትግል በላይ ሰይሞ ሊሰግድለት ወይ ሊሰግድላት እምነቱም ታሪኩም አይፈቅድለትም:: ለወያኔ ያደሩትንና ተለጣፊዎችን ደግሞ ይቃወማል፤ያጋልጣል እንጂ ሌላ አቅዋም ሊኖረው አይችልም:: ታሪክ ይጠቀስ ከተባለም ኢሕአፓ ለማንም አገዛዝ ለጥቅመናሰ ለሹመት ሲል ሕዝብን ከድቶ አላደረም:: ገና ከእንጭጩም የጠባብ ብሄረተኞችን አቅዋምና የግንጠላ መርህ ግብር ተቃወመ እንጂ በርኩስ ተልዕኮአቸው ሹመኛ፤የጎጥ ድርጅት መስራች ወዘተ ሆኖ አላጀባቸውም:: ስንቶቹ ናቸው ይህን ሊሉ የሚችሉ ለመሆኑ?

የሕዝብን ጎራ ለማጠናከርና ሀቀኛ የአንድነት ሀይሎችን አቅም ለመጨመር ከተፈለገ ድክመቶችን ማስወገድ ያስፈልጋል:: በመጀመሪያ ድክመት መኖሩን፤ ድርጅቶችም መሪዎችም ሊሳሳቱ መቻላቸውን ማመን ይገባል:: ይህ ደግሞ በሽፍንፍንና በአትመርምሩ አትተቹ ዕዝ ሳይሆን በጥሞና በሚደረግ ግምገማና ውይይት ላይ መመስረት ያለበት ነው::ከዚህ ቀደም ለመጠቆም እንደተሞከረው ሕዝብ ታጋይ ልጆቹ እንዲያብሩለት ቢፈልግም ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ ያለበት ጊዜ በመረጃ ተደግፎ ሊቀርብ የሚችል አይደለም:: ይህን መፈክር ያሰሙን ዛሬ ተሰባብረው ከወያኔ የተባበሩ መሆኑንም አይተናል::አንድነት ሀይሎች መተጋገዝ ይገባቸዋል፤ ተጋግዘዋልም:: ከዚህ ሌላ ግን ሊደጋገፉ የሚችሉት አንዱ የሌላው ዓይን ሲሆንና ድክመትን ሲጠቁም ሲጠቋቀሙ ነው:: ገንቢ በሆነ ሂስ የምንለው ነው እኛ:: ከዚህ ባሻገር ግን በአቅዋም መሰረታዊ ልዩነት ብቻ ሳይሆን ከበድ ያለ ቅራኔ ካለ ደግም ሸፋፍኖ ማለፍ የሚቻል አይደለም::አንዳንድ ጊዜ ያለው ልዩነት ይዘቱና ስፋት ግልፅ የማይሆንላቸው ሊኖሩ ይችላሉ:: በወያኔ ፓርላማ ገብቶ መታገልና አለመታገል ቀላል ልዩነት አይደለም:: በመጪው ምርጫ ወያኔን ለማጀብ መነሳት አለመነሳት ከባድ ልዩነት ነው:: ከወያኔ ተቃቅፈን እንስራ ባዮችና ወያኔ ጠላት ነው በሚሉት መሀል ያለው ልዩነት እንዲሁ መሰረታዊ ነው:: ሽፍንፍኑ አለባብሰው ቢያርሱን ያስከትላል:: የድርጅት ምስጢር መጠበቁ እንዳለ ሆኖ--ለዚያውም ብዙውን ጊዜ የባቄላ ወፍጮ ነው--የአቅዋም ልዩነትን በተመለከተ ማቻቻል የሚባለው መሰረታዊ የሆነውን አቅዋም ሊመለከት አይችልም::  የወያኔ ተለጣፊንና  ወያኔ አምላኪን አንጃ መቻል ከቶም አይገባም:: የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታወቃል ነውና ገና ከምስረታው ኢዴፓ የተባለው ቡድን ለሕዝብ አለመበጀቱን ያጋለጡት ላይ ብዙ ዘለፋ መዠጎድጎዱን እናስታውሳለን:: ውሎ አድሮ ግን ሀቁ ሊታወቅ ችሏል:: ለምስጋና የቸኮሉ ለውግዘትም ሮጡ ሆኖ እንጂ ሀቁን ሊያይ ዓይኑን ለከፈተ ሁሉ መረጃዎች ብዙ ጊዜ ስውር አይደሉም:: ዛሬም መድረክና ሰፊ ግንባር በሚል በዚህም በዚያም በአስመሳዮች የሚቀነቀነው ሁሉ ለሕዝብ የሚበጅ ይዘት እንደማይኖረው ግልፅ ነው:: በመሆኑም የሀገርና የሕዝብን ጥቅም አስቀድማለሁ የሚል ሁሉ በሕዝብ ትግል ላይ የሚሸረበውን ማንኛውንም ሴራና የሚቃጣውን ማንኛውንም ጥቃት በጊዜ ማጋለጥና መታገል ግዴታው ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ በሕዝብ እኩልነት ማመንና ግንጠላን መቻል የተለያዩ ናቸው:: የብሄር ድርጅቶች ከወያኔ ጀምሮ በራሳቸው የ " ሕዘባችን ወኪልና ተጠሪ ነን" ብለው ራሳቸውን ይሰይሙና ሲተቹ ተቺውን ፀረ ትግሬ ፀረ ኦሮሞ ብለው አፍ ሊዘጉ ይሞክራሉ:: ይህ ማንንም ሊያስፈራራ የሚችል መሆን የለበትም:: የትግራይን ሕዝብ በጠላትነት የማንጀፈርጅ ብንሆንም የወያኔን አገዛዝ ብሄረሰብ አሰራር፤ይዘትና መሰረት ልንክድ አንችልም:: የኦሮሞ ሕዝብን መብት ብናውቅም የኦነግን ነፃ ኦሮሚያና ኦሮሞ ኢትዮጵያዊ አይደለም አቅዋም የምንቀበለው አይደለም :: ይህ በጠባቦቹና አጃቢዎቻቸው ነፍጠኛ ቢያሰኝ እሰየው እንጂ ሌላ መልስም ሊኖረን አይገባም ማለት ነው:: ራሳችንን ለማፅዳትና ለመጠናከር ስንጥርም ወንጀለኛው ወይም ጥፋተኛው በንስሀ ይቀላቀለን ብንል ቂመኝነት አይደለም:: ትላንት የደርጉ መንግስት መንግስታችን ነው ብለው ነፍጠኛ ያሉትን ሲመነጥሩና ኢሕአፓንም በሽብር ሲጨፈጭፉ የነበሩት ዛሬ ተገልብጠው ብሄረተኛ ሆነናል ብለው በነፍጠኝነት ሲከሱን በዝምታ ልናልፋቸው አንችልም:: ጦርነት እስራባ ችኋለሁ ብሎ መፎከር ብቻ ሳይሆን በደረሰብን ወያኔያዊ በደል ሁሉ ዋና ተዋናይ የነበረው ግለሰብ ዛሬ ከወንጀል ጓደኛው ስለተጣላ ብቻ የሕዝብ አርበኛ ነኝ ሲልና ይቅርታ አልጠይቅም ብሎ ሲገተር ዝም ማለት አይገባንም:: ክርስቶስን ተቀበልኩ አገኘሁት (የሀገራችን ባርናባስ ?) ብሎ ስለ ፍቅር ሊሰብከን የተነሳው ታምራት ላይኔም ቢሆን አሁንም ልቡ ከወያኔ ከበሮ ጋር አብሮ የሚደልቅ እንጂ፤ ወያኔና ሻዕቢያ መጣላታቸው ቅር የሚለው እንጂ ላጠፋሁት ሁሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እጠይቃለሁ ሲል እስካሁን አልሰማንም:: ድርጅቶች የወንጀለኞች መደበቂያ ከሆኑ የድርጅቶቹ ማንነት መቆሸሹ አይቀሬ ነውና ሊታሰብበት የሚገባ ነው:: አጠፋን ማለቱ ግን አሳፋሪ ሆኖ በሰሩት አሳፋሪ ስራ ሁሉ ተኩራርቶና ተሸፋፍኖ መጓዙ ከቀጠለ ልንፀዳና እንታገለዋለን ከምንለውም ጠላት ለመለየትና የተሻለ ለመሆን ያዳግተናል::

ወያኔ ስልጣን ከመያዙ በፊትም ሆነ ከያዘ በኋላ የታገሉትና እየታገሉትም ያሉ ሀይሎች አሉ:: እነዚህን አውግዘውና ተቃውመው ከወያኔ ጋር የተሰለፉና አብረውም በሚታገለው ላይ ሲሳለቁ የነበሩ ዛሬ ነፃ አውጪ ነን ሊሉ ከተነሱ መጀመሪያ ሕዝብን ይቅርታ ጠይቁ መባል አለባቸው:: ሊያዩና ሊማሩ ሲችሉ ከጠላት መሰለፍን የመረጡ ናቸው:: ስንቱ ጀግና ታጋይና አዛውንቱ ሐኪምም ሳይቀሩ ለእስር ሲዳረጉ፤እነ አሰፋ ማሩ፤ተሰፋዬ ታደሰ፤ጋይምና ሌሎች ሲሰዉ እነሱ ከወያኔ ጋር መተቃቀፍና መጨፈርን የመረጡ ናቸው:: ተማርን አወቅን ባይ ስለነበሩም አላወቁ ም ለማለት የሚቻል አይደለም:: ሆዳሞች ከተራበው ሲደባለቁ ብቻችንን በልተን ነበርና ይቅር ታ ይበሉ ማለት ይበዛል? ከአሶሳ እስከ በደኖና አሰቦት አርባጉጉ የፈሰሰው ደም ከንቱ አይደለም :: ወያኔ ያፈሰሰው ደም ሁሉ መና ሊቀር አይችልም:: ያለፈው አልፏል ብሎ በዛሬ ዋና ጠላት ላይ አተኩሮ ለመረባረብ ያለፈውን በተመለከተ ያጠፋው --በተለይም ደም ያፈሰሰው- አጥፍቼ ነበር ማለቱ መቅደም አለበት:: ኢሕአፓ ይህን መርህ ሳይከተል ከግራ ቀኙ አብሮ ለመታገል ያደረገው ጥረት ከሞላ ጎደል የተጠበቀውን ፍሬ አለማስገኘቱ ትምህርታዊ ይሆናል:: ሞት ለኢሕ አፓ ያሉትንም መልሶ ማቀፉ ብቻ ሳይሆን በመሪነት ቦታም በመመደቡ ዛሬ በነዚሁ ግለሰቦች

የደረሰበት የአንጃ ምት ሌላ ጠቃሚ ተመክሮ ነው። የትህትና በትር ያስመታል የተባለው ሀቅ የለውም ማለት አይቻልም።

እውን ለሕዝብና ለሀገር የቆሙትን ከአስመሳዮቹና የነገ ተለጣፊዎች መለየት ያስፈልጋል። በሀቅ ለሀገር የቆሙ ሀይሎች ባመቺው መንገድ ቢተባበሩና ቢተጋገዙ ደግሞ ጠቃሚ ይሆናል። የሀገር ወዳጁ ክፍል ሊጠናከር ይችል ዘንድ በቅድሚያ ራሱን ማፅዳትና ከዚያም የትብብሩንና የትግሉን እንቅስቃሴ በተሻለና ውጤታማ በሆነ መንገድ መቃኘት ይጠበቅብታል። ዘወትር ዋይ ዋይ ጉረሮ ን ያሰለቻል እንዲሉ የማያባራ ቁጭትና የሚደጋገም ሽንፈትን ለማስወገድ ሳልተናልና ራሳችንን በቅድሚያ ጠበቅ እናድርግ። በጠላት ላይ እናምርር።